
NUR-
AFRICA
ACADEMY

አማርኛ ቋንቋ 3ኛ ክፍል

የስርዓተ ነጥብ አይነቶች

1. አንድ ነጥብ /ይዘት/ (.) ሙሉና ሽርፍራፊ ቁጥሮች ይለያል።

ምሳሌ፡- 3.4 (ሶስት ነጥብ አራት)

- ብርን ከሳንቲም ይለያል።

ምሳሌ 5.25 ሳ (አምስት ብር ከሃያ አምስት ሳንቲም)

- ቃላትን በምህፃረ ቃል አሳጥሮ ለመፃፍ ያገለግላል።

ምሳሌ አ.አ = አዲስ አበባ



2. ሁለት ነጥብ (፡) ሰዓትን ከደቂቃ ይለያል።

ምሳሌ፡- 7፡10 (ሰባት ሰዓት ከአስር)

- ቃልን ከቃል ይለያል።

ምሳሌ፡- ልጅቷ፡ጎበዝ፡ተማሪ፡ናት።

3. አራት ነጥብ (።) በዓ.ነገር መጨረሻ በመግባት ዓ.ነገርን ይቋጫል።

-ዓ.ነገሩን ማለቁን ወይም መጠናቀቁን ያመለክታል።

ምሳሌ፡- 1 አንበሳ የዱር እንስሳ ነው።

4. የጥያቄ ምልክት /ትዕምርተ ጥያቄ (?)

- በመጠይቃዊ ዓ.ነገሮች መጨረሻ ላይ በመግባት ዓ.ነገሮቹ መልስ የሚፈልጉ መሆናቸውን ያመለክታል።

ምሳሌ፡- 1. ምን ትወጃለሽ ?

2. አህመድ ከገጠር መቼ መጣ ?

5. ቃለ አጋኖ /ትዕምርተ አንክሮ (!)

- ግነትን፣ ደስታን፣ ቁጣን፣ አድናቆትን ወዘተ የመሳሰሉትን ውስጣዊ ስሜታችንን ለመግለፅ ያገለግላል።

ምሳሌ፡- 1. ልጅቷ የሰራችው ዶሮ ወጥ ጣት ያስቆረጥማል። (ግነትን)

2. ጥፋ ከፊቴ! (ቁጣን)

3. ዋው! አባቴ የገዛው መኪና በጣም ያምራል።(አድናቆትን)

6. ነጠላ ሰረዝ (፣)

- ተከታትለው የመጡ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው የቃላት ድርጅቶችን ለመለየት ያገለግላል።

ምሳሌ፡- ሲሃም ደብተር፣እስክርቢቶ፣እርሳስና መቅረጫ ገዛች።